# የሠርክ ጸሎት

**የመክፈቻ ጸሎት፤ ውዳሴ ማርያም ይደገማል**

## የቅዱስ ጎርጎርዮስ ጸሎት

አምላካችን እግዚአብሔር የሰውን ሁሉ ሕሊና የምታውቅ ልቡናን ኩላሊትን የምትመረምር። ያንተ በሚሆን በዚ ህ ቅዱስ ቦታ አገለግል ዘንድ ሳይገባኝ ጠርተኸኛልና። ቸል አትበለኝ ፊትህንም ከኔ አትመልስ ኃጢአቴንም አር ቅልኝ እንጂ፤ በነፍስ በሥጋ ከሠራሁትም ኃጢአት አንጻኝ።

አሁንም የኔን ኃጢአትና የሕዝቡንም በደል ይቅር ትል ዘንድ አልምንሃለው፣ እማልድሃለው። ወደ ፈተናም አታግ ባኝ። አቤቱ አትጣለኝ ተስፋዬን ነሥተህ አታሳፍረኝ፤ የመንፈስ ቅዱስን ሀብት አሳድርብኝ እንጂ በቤተ መቅደስ ህ እቆም ዘንድ ኃጢአቴንና በደሌን ለማስተሥረይ በቅን ልቡና ንጹሕ መስዋዕትን አቀርብልህ ዘንድ የበቃሁ አድ ርገኝ።

የሕዝብህንም ኃጢአት አታስብባቸው፤ ለሞቱት አባቶቻችን ለወንድሞቻችን ለእኅቶቻችን ዕረፍትን ስጥ። ሕዝብ ህን በከሃሊነትህ አጽንተህ ጠብቃቸው፤ ከአንድ ልጅህ ጋራ ላንተ ምስጋና ይገባልና፤ ለዘላለሙ። አሜን።

## ሊጦን

ይ.ካ. በኪሩቤል አድረህ የምትኖር አምላካችን ሆይ በመላእክት ዘንድ ትከበራለህ ትመሰገናለህ። የተቀደሰ ማደሪ ያህ ከሆነ አዳራሽ አንገባ ዘንድ ያደልከን አንተ ነህ። የምስጋናህን ቅድስና እናስብ ዘንድ።
የማታውን ምስጋና እናቀርብልህ ዘንድ የሁላችንን መማጠን ተቀበል። ሰማያዊ ምስጢርህን በምናስብበትእምነት ረ ብህ ጥቅምን ስጠን። ሁላችንንም ያለመጨነቅ ያለ መሸነፍ ያለ መሰናከል ጠብቀን፤ እግሮቻችንን ከድጥ፤ ዓይኖ ቻችንን ከዕንብ፤ ሰውነታችንን ከኃጢአት ሞት አድነን። ከቀድሞ ጀምሮ ያገለገሉህን የወዳጆችህን ሁሉ ልመና አስበህ በአንተ ከዳኑት ጋር ቍጠረን።

በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም።

ይ.ሕ. አሜን

ይ.ካ. ሁሉን የሚይዝ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን። ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔርን በሁሉ ለተመሰገነና ለተደነቀ ስሙ እንዘምር እናመሰግን ዘንድ፤ በተመሰገነው በዚህ ቦታ እንድንቆም ዳግመኛ ደስታን ሰጥቶናልና። ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔርን ነው።

ይ.ዲ. ጸልዩ

ይ.ሕ. በዚህ ጊዜ ሕዝቡ አባታችን ሆይ ይበሉ።
ይ.ካ. ሁሉን የምትይዝ ጌታ ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለን፤ በመላው ሌሊት እንደጠበከን ወደ ቀኑም ብርሃን ዳግመኛ እንዳደረስከን በሚመጣው ሌሊት ጠብቀን። ፍቅርን ያለ ኃጢአት በሠርክና በሌሊት ስጠን። ከሌሊት ፍ ርሃት ወደ ጨለማም ከሚወስድ ኀዘን አድነን፤ ከዓመፀኛና ከሀሰተኛ ሰውም ተበጀን። ሰው እንደመሆናችን የበደ ልነውን የተሰወረውን ይቅር በለን። አንተ እግዚአብሔር ቸር ሰው ወዳጅ ነህና።

በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለ ሙ።

ይ.ሕ. አሜን

## ከቅዱስ ያሬድ የዜማ መጽሐፍ የተቀዳ

አድኅነነ ሕዝበከ፤ ወባርከነ ርስተከ ሀበነ ኀይለ ወመዊዐ ለአግብርቲከ ለእለ ንጼውዕ ስመከ፤ ዕቀበነውሉደ ሕዝበከ፣ ወሕፅረነ በኃይለ መላእክቲከ ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት። በኀይለ መስቀልከ ርድአነ በዕፀ መስቀልከ ቤዝወነ።

እኛን ወገኖችህን አድነን፤ የጥንት ተገዥዎችህንምባርከን፤ ስምህን ለምንጠራ ለኛ ለአገልጋዮችህ ድል መንሳትንና ኃይልን ስጠን። የወገኖችህን ልጆችእኛን ጠብቀን፤ በየጊዜውና በየሰዓቱ በመላእክት ታዳጊነት በውስጥ በአፍአ ጠብቀን። በመስቀልህ ታዳጊነት ርዳን በመስቀልህ ተቤዠን።

በእንተ አብርሃም ፍቁርከ ወበእንተ ይስሐቅ ቍልኤከ ወበእንተ እስራኤል ቅዱስከ ተዘከር እግዚኦ ኪዳነከ። ፍጡነ ፈኑ ሣህለከ መሐር ኪያነ ዘፈጠርከ። ሥረይ ኃጢአተ ሕዝብከ ወመሐር ተግባረከእግዚኦ ኢታጥፍአነ ሐሰ ለከ።

ስለ ባለሟልህ አብርሃም፤ ስለ ወዳጅህ ስለ ይስሐቅ ስለ መረጥከው ስለ እስራኤልም ብለህ አቤቱ ቃል ኪዳንህን አስብ። ይቅርታህን ፈጥነህ ላክ የፈጠርኸን እኛን ማረን። የወገኖችህን ኃጢአት አስተሥርይ የእጅህን ፍጥረቶች እኛን ማረን፤ አቤቱ አታጥፋን፤ ይህ በአንተ ዘንድ አይደረግ።

በእንተ ማርያም ወላዲትከ ወበእንተ ዮሐንስ መጥምቅከ። ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ ርድአነ ወትረ በኀይለ መስቀልከ፤ ኢታስተኃፍረነ እግዚኦ በቅድሜከ።

በእናትህ በማርያም አማላጅነት፤ በአጥማቂህ በዮሐንስና በቅዱሳንህም ሁሉ አማላጅነት ሁል ጊዜ በመስቀልህ ታዳጊነት ርዳን፤ አቤቱ በፊትህ አታሳፍረን።

እግዝእትነ ነጽሪ ኀቤነ ጸሌዪ ለነ ለደቂቅኪ ወአድኅነነ እምኵሉ ምንዳቤ ወኀዘን።

እመቤታችን ሆይ ወደኛ ተመልከቺ፤ ለእኛ ለልጆችሽ ለምኚልን፤ ከችግርና ከኀዘን ሁሉ አድኚን።

መዐልተ ምስሌነ ወሌሊተ ማእከሌነ አንተ እግዚኦኢትርኃቅ እምኔነ ሀሉ ምስሌነ ረዳኤ ኩነነ ኢትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላከ ሰላም ተራድአነ።

ቀን ከኛ ጋር ሌትም በመካከላችን ሁን። አቤቱ አንተ ከኛ አትለይ። ከኛ ጋር ኑር፤ ረዳትም ሁነን፤ አትተወን አትናቀንም፤ የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን።

ኢትግድፈነ ኢትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላከ ሰላም ተራድአነ። (3ጊዜ)

አትተወን አትተወን አትናቀንም፤ የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን። (3ጊዜ)

እግዝእትነ እግዝእትነ ነጽሪ ኀቤነ ሰላመ ወልድኪ የሀሉ ምስሌነ። (3ጊዜ)

እመቤታችን ሆይ እመቤታችን ሆይ ወደኛ ተመልከቺ፤ የልጅሽም ሰላም በኛ ላይ አድሮ ይኑር። (3)



**ሃሌ ሉያ፤** ዘበእንቲሃ ለቤተ ክርስቲያን ተጸፋእከ በውስተ ዐውድ፤ ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር።

**ሃሌ ሉያ፤** ለቤተ ክርስቲያን ስትል በአደባባይ በጥፊ የ ተመታህ አቤቱ ይህን ማድረግህ እርስዋን በከበረ ደምህ ትቀድሳት ዘንድ ነው።

ዘበእንቲሃ ዝግሒታተ መዋቅሕት ያረ። ወተዐገሠ ምራቀ ርኩሰ እንዘ አልቦ ዘአበሰ፤ **አምላክ** ዲበ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ።

ስርስዋ ሲል ታስሮ መጐተትን የቻለ፤ የበደለውን በደል ሳይኖር ርኩስ ምራቅን ሲተፉበት የታገሰ **አምላክ** በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ።

ከቅዳስ ያሬድ ጸሎት

**ሃሌ ሃሌ ሉያ** አርእየነ እግዚኦ ሣህለከ፤ ረዳኤ ኩነነ ወኢትግድፈነ፣ መሐረነ መሐከነ እግዚኦ እግዚኦ ተሣሃለ ነ።

**ሃሌ ሃሌ ሉያ** አቤቱ ይቅርታህን አሳየን፤ እርዳን አትተ ወን፤ አቤቱ ማረን ይቅር በለን።

---

## የምህላ ጸሎት

| | |
|---|---|
| **መሐረነ አብ** | **አብ** ሆይ ማረን |
| *–ሃሌ ሉያ* | *ሃሌ ሉያ* |
| **ተሣሃለነ ወልድ** | **ወልድ** ሆይ ይቅር በለን |
| *–ሃሌ ሉያ* | *ሃሌ ሉያ* |
| **መንፈስ ቅዱስ** መሐሪ ተዘከረነ በሣህልከ። (3ጊዜ) | ይቅር ባይ **መንፈስ ቅዱስ** ሆይ በይቅርታህ አስበን |
| *–ለከ ንፌኑ ስብሐተ ወለከ ናዐርግ አኰቴተ።–* | *ለአንተ ፍጹም ምስጋናን እናቀርባለን።* |
| *መሐረነ መሐሪ ኃጢአተነ አስተሥሪ* | ቸር ይቅር ባይ ሆይ ማረን ኃጢአታችንንም አስተሥርይ ልን |
| *–ወአድኅነነ* | |
| *ወተማኅፀን ነፍሰነ ወሥጋነ* *–**ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር።*** | **የእግዚአብሔር** ልጅ **ኢየሱስ ክርስቶስ** ሆይ አድነን በነፍስም በሥጋም ጠብቀን። |

| | |
|---|---|
| አምላክነ | አምላካችን |
| *–ወመድኃኒነ* | *መድኃኒታችን* |
| ኢየሱስ ክርስቶስ ተሣሃለነ። | ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን። |
| *–በብዝኃ ምሕረትከ* | *በቸርነትህ ብዛት* |
| ደምስስ አበሳነ | በደላችንን ደምስስ |
| *–ወፊኑ ሣህለከ ላእሌነ።* | *ይቅርታህንም ላክልን።* |
| እስመ እምኀቤከ | ይቅርታ ካንተ ዘንድ ነውና |
| *–ውእቱ ሣህል* | |
| ሃሌ ሉያ መሐረነ አብ መሐሪ | ሃሌ ሉያ ይቅር አብ ሆይ ማረን። |
| *–ወተሣሃለነ* | *ይቅር በለን።* |
| ሀብ ሣህለከ መሐሪ | መሐሪ የሆንህ አቤቱ ይቅርታን ስጠን፤ |
| *–ኢታጥፍአነ ተዘኪረከ ዘትካት* | *የቀድሞ ኃጢአታችንንም አስበህ አታጥፋን።* |
| በምሕረትከ | በቸርነትህ |
| *–እስመ መሐሪ አንተ* | *አንተ ይቅር ባይ ነህና* |
| ወብዙኅ ሣህልከ ለኲሎሙ እለ ይጼውዑከ። | ለሚጠሩህ ለሚለምኑህ ሁሉ ይቅርታህ ብዙ ነው። |
| *–ይጼውዑከ በጽድቅ* | *በእውነት ይጠሩሃል* |
| ሰማዒ ወትረ | አንተም ዘወትር ትሰማለህ |
| *–ከሃሊ ዘውስተ አድኅኖ።* | *ሁሉን ለማድረግ የምትችል ነህ።* |
| ከሃሊ<br>*- ዘውስተ አድኅኖ።* | ሁሉን ለማድረግ የሚችል |
| –ለአምላክነ እስመ ጽድቅ ቃሉ። | የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና። |
| *ንስአሎ ለአብ* | ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ አብን እንለምነው። |
| –ይፊኑ ለነ ሣህሎ | |
| *እስመ አብ የአክል ለዘሰአሎ* | አብ ለለመነው ሁሉ ይበቃልና። |
| –ሃሌ ሉያ | ሃሌ ሉያ |
| *ሰብሐት ሎቱ ይደሉ* | ለርሱ ምስጋና ይገባል። |

*–ሃሌ ሉያ አኮቴት ሎቱ ይደሉ*

ሃሌ ሉያ

*–ለክርስቶስ ለእግዚአ ኵሉ*

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ

*–ወይእዜኒ*

መኑ ተስፋየ

*–አኮኑ*

እግዚአብሔር

*–ውስተ እዴከ አግዚኦ አመኅፅን ነፍስየ*

ኀበ አምላከ ምሕረት

*–አመኅፅን ነፍስየ*

ኀበ ንጉሠ ምሕረት

*–አመኅፅን ነፍስየ*

በእግዚእየ ወአምላኪየ

*–አመኅፅን ነፍስየ*

እምኵሉ ምግባረ እኩይ አድኅና ለነፍስየ።

*–ሀቡ*

ንስአሎ

*–ንስአሎ*

ወናስተምሕሮ

*–ለአምላክነ ጻድቅ እስመ ጽድቅ ቃሉ።*

ዘይክል ኵሎ በአልቦ ዘይሰአኖ

*–አምላከ ነዳያን ወተስፋ ቅቡጻን*

ንሕነ ኀቤከ ተማኅፀነ። (3ጊዜ)

ሃሌ ሉያ ለርሱ ክብር ምስጋና ይገባል።

ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሉያ ለሁሉ ጌታ ለክርስቶስ

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ

ዛሬስ ተስፋዬ ማነው?

እግዚአብሔር አይደለምን?

አቤቱ ነፍሴን ላንተ አደራ አስጠብቃለሁ

ከምስጋና አምላክ ዘንድ

ነፍሴን ላንተ አደራ አስጠብቃለሁ

ከምሕረት ንጉሥ ዘንድ

ነፍሴን ላንተ አደራ አስጠብቃለሁ

በጌታዬና በአምላኬ

ነፍሴን ላንተ አደራ አስጠብቃለሁ

ከክፉ ሥራ ሁሉ ነፍሴን (ሰውነቴን) አድናት።

ኑ

እንለምነው

እንለምነው

እንማልደው

የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና።

ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው

የድሆች አምላክ ተስፋ ላጡ

ተስፋቸው የምትሆን አቤቱ! እኛ ወዳንተ ተማጥነናል

*ወበከመ ዐቀብከነ እምነግህ እስከ ሠርክ እቀበነ እግዚኦ እምሠርክ እስከ ነግህ። (3ጊዜ)*

ከጧት እስከ ማታ እንደ ጠበቅኸን አቤቱ እንዲሁከማታ እስከ ጧት ጠብቀን። (3ጊዜ)

ተማኅፀልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ ስማዕ ጸሎተነወስእለተነ ወስረይ ኵሎ ኃጢአተነ ስማዕ ጸሎተነ ዘሰማዕኮ ጸሎቶ ወስእለቶ ለዕዝራ፤ ተወከፍ ምህላነ ሰላመከ ሀበነ፤ እማእከሌነ ኢትርኀቅ።

ሃሌ ሉያ አቤቱ ምድርህን ይቅር አልክ። ጸሎታችንና ልመናችንን ስማ። ኃጢአታችንን አቃልልን (ይቅር በል) የዕዝራን ጸሎትና ልመናን የሰማህ (አምላክ) የእኛንም ጸሎት ስማ ምህላችን ተቀበል፤ ሰላምህን ስጠን ከመካከላችንም አትራቅ (ከእኛ አትለይ)።

*ወሚጥ መዐተከ እምኔነ ሃሌ ሉያ ንዒ ሀቤየ እንቲአየ ሠናይት ርግብየ መዓዛ አፉሀ ከመ ኮል ወኵሉነገረ ሰላም።*

*ሃሌ ሉያ መዓትህን ከእኛ መልስ። መልካሟ ርግቤ የእኔ ሆይ ወደ እኔ ነዩ። የአፏ መዓዛ እንደ እንኮይ ነው። ነገሯም ሁሉ በሰላም ነው።*

አርእየነ እግዚኦ ሣህለከ ሃሌ ሉያ መልአከ ሰላምነሊቀ መላእክት ሚካኤል ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ፤አእርግ ጸሎተነ ቅድመ መንበሩ ለንጉሥ ዐቢይ።

ሃሌ ሉያ አቤቱ ይቅርታህን አሳየን የሰላማችንን መልአክ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሆይ ስለ እኛፈጽመህ በምንልን። ከታላቁ ንጉሥ ከመንበሩ ፊት ጸሎታችንን አሳርግልን።

*ገብርኤል አብሰራ ለማርያም ወይቤላ ትወልዲ ወልደ፤ ወይነግሥ ለቤተ ያእቆብ ለዓለም፤ ወአልቦ ማሕለቅት ለሰላሙ።*

*ማርያምን ገብርኤል አበሰራት እንዲህም አላት። ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ለያዕቆብ ቤት ለዘለዓለሙ፡ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።*

ሰአል ለነ ጊዮርጊስ ኀበ እግዚአብሔር ወጸሊ በእንቲአነ፤ ሀረድዎ ገመድዎ፣ ወዘረው ሥጋሁ ከመ ሀመድ፣ ወወሰድዎ ሀበ ፸ ነገሥት ረገጸ ምድረ አንስአ ሙታን አባ ጊዮርጊስ በሰላም ዐደወ መንግሥተ ክብር ወረሰ።

ጊዮርጊስ ሆይ ወደ እግዚአብሔር ስለ እኛ ለምንልን። አርደው ከፋፋሉት ሥጋውንም እንደ ትቢያበተኑት ወደ ፸ ነገሥታት ወሰዱት። ምድርን ረገጠ ሙታንን አስነሳ። አባ ጊዮርጊስ በሰላም (በጽናት) ተሸጋገሮ የክብር መንግሥትን ወረሰ።

*ባርከኒ አባ እንሳእ በረከተከ በእንተ ሰላማ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን አባ ባርከኒ እንሳእ በረከተከ።*

*አባ በረከትህን እቀበል ዘንድ ባርከኝ ፤ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ስትል በረከትህን እቀበልዘንድ ባርከኝ።*

ብፄዕ አባ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘኤለ ገዳማተ እምሀበ እግዚኡ ይንሳእ እሴተ፤ ቦአ ሀገረ ደብረ ሊባኖስ በፍሥሐ ወሰላም።

ከጌታው ዋጋን ይቀበል ዘንድ በበርሐ የተንገላታ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ንዑድ ነው ክቡር ነው።በሰላም በደስታ ወደ ደብረ ሊባኖስ ገባ።

*ማህደረ ሰላምነ ቅድስት ደብተራ እሞሙ ለሰማእት ወእህቶሙ ለመላእክት ንዑ ንስግድ ኵልነ ኀበ ማርያም እምነ።*

*የሰላማችን መገኛ ቅድስት (የተከበረች ድንኳን) ቅድስት ማርያም ናት። የሰማእታት እናታቸው የመላእክት እህታቸው ናት። ከእናታችን ማርያም ፊት ሁላችን እንሰግድ ዘንድ ኑ።*

መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተ ክርስቲያን ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም ሰላመከ ሀበነ።

ለዓለም ሁሉ መስቀል ብርሃን ነው። የቤተ ክርስቲያን መሠረት እርሱ ነው። ሰላምን የሚሰጥ ዓለምንየተቤዠህ (አምላክ) ሆይ ሰላምህን ስጠን።

*ሰላመ አብ ወሰላመ ወልድ ወሰላመ መንፈስ ቅዱስ የሃሉ ማእከሌክሙ አኀው።*

*የአብ ሰላም የወልድ ሰላም የመንፈስ ቅዱስ ወገኖች (ወንድሞች) ሆይ ከእናንተ ጋር ይሁን።*

ይ. ካ. ሰላም አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወፍቅራ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ሞገሰ መስቀሉ ወሀብተ ረድኤቱ የሃሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ (5 ጊዜ
በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ (5 ጊዜ)

አቤቱ ይቅር በለን
ስለ እናትህ ማርያም ብለህ ይቅር በለን።

ሰአሊ ለነ ማርያም ምሕረተ ወልድኪ የሐውጸነ ማርያም። ሰአሊ ለነ ማርያም ለለሰዓቱ ተግባረ እደዊሁ ለወልድኪ ኢንጥፋ በከንቱ። ኵሎ መዓልተ ወኵሎ ሌሊተ ብዙኃ ኃጢአተ ዘገበርነ በእንተ ማርያም እምከ ተማኅፀነ። ሥመር እግዚኦ ከመ ታድኅነነ።ኢታርምም እግዚኦ ወኢትጸመመነ ተዘከር እግዚኦከመ መሬት ንሕነ። እግዚኦ ዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ። እግዚኦ ዕቀባ ለመካንነ ......። እግዚኦ አእርፍ ነፍሳተ አግብርቲከ ወአእማቲከ ኵሎሙ ክርስቶሳውያን።

ማርያም ሆይ የልጅሽ የእጁ ሥራ የሆን እኛ በከንቱ እንዳንጠፋ በየሰዓቱ ለምኚልን። በቀኑ ሁሉ፣ በሌሊቱም ሁሉ የሠራነውን ብዙ ኃጢአት ይቅር ትል ዘንድ በእናትህ በማርያም ተማፅነናል። አቤቱ ታድነን ዘንድ ውደድ ዝም አትበል። አቤቱ ቸል አትበለን። ከመሬት (አፈር) የተፈጠርን መሆናችንን አስብ። አቤቱ ሀገራችን ኢትዮጵያን ጠብቃት።አቤቱ ቦታችንን . . . ጠብቃት። አቤቱ የባሮችህንየወንዶችንና የሴቶችን ነፍስ አሳርፍ።

## የሃይማኖት ጸሎት

ሁሉን በያዘ ሰማይንና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋራ በነበረ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም እናምናለን። — ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፤ የተፈጠረ ያይደለ የተወለደ፤ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል። ሁሉ በእርሱ የሆነ ያለ እርሱ ግን ምንም የሆነ የለም በሰማይም ያለ በምድርም ያለ። – ስለኛ ስለሰው ስለመዳናችን ከሰማይ ወረደ። ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ከቅድስት ድንግል ማርያምም ፈጽሞ ሰው ሆነ።— ሰው ሆኖ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ። ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረም፤ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በቅዱሳት መጻሕፍትእንደ ተጻፈ።– በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ።— ዳግመኛ ሕያዋንን ሙታንንምይገዛ ዘንድ በጌትነት ይመጣል። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።— ጌታ ማኅየዊ በሚሆን ከአብ በሠረጸበመንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እንሰግድለት እናመስግነው ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋራ በነቢያት የተናገረ።— ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን። ኃጢአትን ለማስተስረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።— የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን፤ የሚመጣውንም ሕይወት ለዘላለሙ፤ አሜን።

## ጸሎተ ወንጌል

ይ. ዲ. ተንሥኡ ለጸሎት
ይ. ሕ. እግዚኦ ተሣሀለነ
ይ. ካ. ሰላም ለኵልክሙ
ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ

ይ. ዲ. ለጸሎት ተነሡ
ይ. ሕ. አቤቱ ይቅር በለን
ይ. ካ. ሰላም ለሁላችሁ ይሁን
ይ. ሕ. ከመንፈስህ ጋር (እንደ ቃልህ ይደረግልን)

ይ. ካ. አቤቱ አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና ንጹሐን ሐዋርያትን እንዲህ ያልካቸው፤ እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙ ነቢያት ጻድቃን ወደዱ አላዩም፤ እናንተ ዛሬ የምትሰሙትን ይሰሙ ዘንድ ወደዱ አልሰሙም። የእናንት ያዩ ዓይኖቻችሁና የሰሙ ጆሮቻቹህ ግን የተመሰገኑ ናቸው። እኛንም እንደነሱ የበቃን አድርገን በቅዱሳን ጸሎት የከበረ የወንጌልን ቃል ሰምተን እንሠራ ዘንድ።

ይ. ዲ. ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱስ
ይ. ሕ. ይረስየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱሰ

ይ. ዲ. ክቡር ስለሚሆን ወንጌል ጸልዩ
ይ. ሕ.የከበረ ወንጌልን ለመስማት የበቃን አድርገን

**የዕለቱን ምስባክ በል፤-**

ይ. ዲ. ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ወንጌል ቅዱስ ዜናሁ ለእግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ይ. ዲ. ሃሌ ሉያ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱስ ወንጌልን ቆማችሁ ስሙ።

ይ. ካ. (በልዑል ዜማ) ወንጌል ቅዱስ
ይ. ሕ.ስብሐት ለከ ክርስቶስ እግዚእየ ወአምላኪየ ኵሎ ጊዜ።

ይ. ካ. (በታላቅ ዜማ) ወንጌል ቅዱስ
ይ. ሕ. ጌታዮና አምላኬ ክርስቶስ ሆይ፤ ሁል ጊዜ ላንተ ምስጋና ይገባል።

## ጸሎተ ኪዳን

ይ. ካ. ቅዱስ

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሀለነ እግዚኦ።

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት። ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ። አቤቱይቅር በለን።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፤ ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሀለነ እግዚኦ።

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት፤በዮርዳኖስ የተጠመቀ በመስቀል ላይ የተሰቀለ።አቤቱ ይቅር በለን።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት፤ ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት እለት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ተሣሀለነ እግዚኦ። ስብሐት ለአብ፣ ስብሐት ለወልድ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን ወአሜን፤ ለይኩን ለይኩን።

እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት፤ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሣ። በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ ተቀመጠዳግመኛም በጌትነት ይመጣል፤ በሕያዋንም በሙታን ይፈርድ ዘንድ፤ አቤቱ ይቅር በለን። ለአብ ምስጋና ይገባል፣ ለወልድ ምስጋና ይገባል፣ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል፣

ይ. ካ. ጸጋሁ ለእግዚአብሔር የሀሉ ምስሌክሙ።
ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ
ይ. ካ. አእኵትዎ ለአምላክነ
ይ. ሕ. ርቱዕ ይደሉ

ይ. ካ. የእግዚአብሔር ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።
ይ. ሕ. ከመንፈስህ ጋር (እንደ ቃልህ ይደረግልን)
ይ. ካ. አምላካችንን እናመስግነው።
ይ. ሕ. እውነት ነው ይገባል።

ይ. ካ. የማትለወጥ አንተን አብን የነፍሳችን መድኃኒት የምትሆን የጥበባት መሠረት የልቡናችን ጠባቂ።ውሳጣዊ ዓይናችንን ብሩህ ያደርግህልን። የሕሊናችንን ጨለማ አርቀህ ከአንተ በሚገኝ ዕውቀት አከበርከን ለጥፋት የተሰጠ የቀደመ ሰው አዳምን በልጅህ መስቀል አዳንህ በማይለወጥ አደስከው ስሕተቶች በትእዛዝህ ጠፉ በልጅህ ሞት አዳንህ። የጠፋውን ፈለግህ።
ይ. ሕ. ንሴብሐከ እግዚኦ (አቤቱ አንተን እናመሰግናለን)

ይ. ካ. ሳናቋርጥ አርምሞ ጽርዓት በሌለበት ቃል ሊቃነ መላእክት ለሚያመሰግኑህ ለአንተ ከምስጋና የሚበልጥ ምስጋናን እናቀርብልሃለን። ያውም መላእክት የሚያመሰግኑት ምስጋና ነው። አቤቱ አንተን በማኅሌት ያመሰግኑሃል። ያንተ ምክር፣ ያንተ ቃል፣ ያንተ ጥበብ፣ ያንተ መጐብኘት የላክኸውን ወልድ ከቀድሞ ጀምሮ ካንተ ጋር የነበረ፤ ዓለም ሳይፈጠር ያልተፈጠረ፤ ባሕርየ ሰብእን ለማዳን በሥጋ የተገለጸቃል ልጅህ ወዳጅህ ጌታችን ኢየሱስ ከኃጢአት ቀንበር ነጻ አደረገን። አቤቱ ስለዚህ እኛ አገልጋዮችህእናመሰግንሃለን።
ይ. ሕ. ንዌድሰከ እግዚኦ (አቤቱ አንተን እናመሰግናለን)

ይ. ካ. ምስጋናን ሦስተኛ ጊዜ ከልባችን ለአንተ እናቀርባለን። ሕይወትን የምትሰጥ አቤቱ። የትሁታንን ሰውነት የሚጐበኝ የተቸገረውን ሰውነት ቸል የማይል። ከሀገራቸው የተሰደዱትን የሚቀበላቸው የሚረዳቸው። በመከራ ያ

ሉትን የሚያድን ለተራቡት የሚያስብላቸው ለተበደሉ የሚበቀልላቸው። የምእመናን ወዳጅ ለጻድቃን የሚመሰክርላቸው የንጹሐን ማደሪያቸው፤ በእውነት የሚለምኑትን የሚሰማ ባልቴቷን የሚሠወር አባት እናት የሞቱበትን የሚያድን የሃይማኖት ክብር ምስጋና ማረፊያ ላደረጋት ለቤተ ክርስቲያን ቅን መሪ የሚሰጥ። ሀብት ጸጋ ኃይልም የመንፈስ ቅዱስ ጉባኤ የምትሆን።

አንተ ስናመሰግን ዘወትርም ሳናርፍ የመንግሥትህን ነገር በልቡናችን እናውቃለን። አንተ ስለ ገለጽህልን፤ልጅህ ወዳጅህ ጌታችን ኢየሱስም ስለ ገለጸልን ምስጋና ጽንዕ ያለው ለዘላለሙ።
ይ. ሕ. አሜን

## ተፈጸመ ጸሎተ ሠርክ ዘዘወትር።

## የኢትዮጵያ መዝሙር

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን ረስቼሽ እንደሆን ቀኜ ትርሳኝ።

ያላሰብሁሽ እንደሆን ምላሴ በትናጋዬ ይጣበቅ፤

ከደስታዬ ሁሉ በላይ ኢትዮጵያ ሆይ ከፍ ከፍ ባላደርግሽ፤

አቤቱ ፈጣሪያችን በኢትዮጵያ ቀን የጠላቷን ልጆች አስብ፤

አፍርሷት አፍርሷት እስከ መሠረቷ ድረስ አፍርሷት ያሏትን፤

አንቺ የተፈታሽ የጠላታችን ልጅ ያደረግሽብንን ብድራት የሚመልስብሽ አምላካችን የተመሰገነ ነው።

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን ረስቼሽ እንደሆን ቀኜ ትርሳኝ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

~~~~~~~~~//~~~~~~~~~~~

በ1936 ከታተመው የቤተ ክርስቲያን ጸሎት ከሚለው የተወሰደ።
~~~~~~~~~